★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ልዩ ዕትም ሚያዝያ 1/ 1999

# 1964--1999

# ኢሕአፓ 35 ዓመት

# ሐሳቡ ትልቅ፣ ነገሩ ጥልቅ

*ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር ለ35 ዓመት ቃል ኪዳንን አክብሮ፣ ውጣ ውረዱን ችሎ፣ በአገሪቱ ላይ የአፈናው ጭጋግ ባልገለጠበትና ጨለማው ባጠላበት ሁኔታ ብሩህ ኢትዮጵያን አይቶ፣ የተቃወመ ውጉዝ ተብሎ መቀመቅ በሚወርድበት፣ ዙሩያ ገባውን ገምግሞ፣ ፀንቶና በርትቶ መታገል ቀላል ጉዳይ አይደለም:: ድርጅትን ራሱን አቆይቶ መገኘቱ ከባድ መሆኑን በፖለቲካው አድማስ ብቅ እያሉ እልም ካሉት በርካታ ቡድኖች ሁኔታ ማወቅ÷ መመዘን የሚቻል ነው:: ኢሕአፓ የራሱን አቃቂር÷ የራሱን መልክና ጠባይ ይዞ የተጓዘ ድርጅት ቢሆንም በ35 ዓመት አውደ ሂዱቱ፣ ማነህ የሚለውን ጥያቄ ለሚጠይቅ ሁሉ የመጀመሪያ መልሱ ሕዝባዊ÷ ኢትዮጵያዊ የሚለው ምን ጊዜም ተቀይሮ አያውቅም::*

*ኢሕአፓ በሚያዝያ 1/ 1964 ዓ.ም. የተመሠረተው ምንም ተቃዋሚ ድርጅት በሌለበት፣ ሥርዓቱ ትንፍሽ ማለትን÷ መቃወምን በከለከለበት፣ የጠየቀ÷ የመረመረ መናፍቅ ይባል በነበረበት፣ ተበደልኩ ÷ እንዴት ይህ ተፈፀመ ብሎ ከባለሥልጣን ጋር ሙግት መግባት በማይፈቀድበት፣ በማይቻልበት፣ ቄሱም ዝም መፅሀፉም ዝም ብቻ በሚፈቀድበት አሊያም አማራጩ ለሥርዓቱ ማርገድ ብቻ በሆነበት ሁኔታ ነበር:: ኢሕአፓ ከምስረታው ጀምሮ ሐሳቡ ትልቅ ነገሩ ጥልቅ ሊባል የበቃው የመስራቾቹ ቁጥር በዝቶ አቅሙ ገዝፎ ሳይሆን ይናቅ በነበረው በጭቁኑ ሕዝብ፣ በገባሩና በአርሶ አደሩ÷ በላብአደሩ/ሠራተኛው ላይ አልፎም በሀገር ወዳዱ ላይ ሙሉ እምነትን አሳድሮ÷ እናቸንፋለን ብሎ÷ አምኖና ቆርጦ በመነሳት፣ ለሀገሩና ለሕዝብ መስዋዕትነትን ሊከፍል ደፍሮ በመገኘቱና አርቆ አስተዋይ በመሆኑ ነው:: የማይደፈር÷ የማይገረሰስና መለኮታዊ የተባለውን የአፄውን ሥርዓት አስወግዶ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የዴሞክራሲን ጮራ መፈንጠቅ ይቻላል ያለው ኢሕአፓ ከተወለደበት ተጨባጭ ታሪካዊና ባህላዊ ሁኔታ÷ ከተመክሮ ማነስ÷ ከትግሉ ውስብስብነትና ፈጣን ጉዞ÷ ከነበረው የርዕዮተ ዓለም ግንዛቤም ጥልቀት ወዘተ... አንፃር በግንዛቤም በተግባርም መስኮች ችግሮች አጋጥመውታል:: ተመክሮን አካብቶ፣ ተጨባጭ ሁኔታውንም በበለጠ ጥልቀት መርምሮና ተገንዝቦ፣ የትግል ስምሪቱንም በተመለከተ በቂ መሠረት ጥሎ ከመጓዙ በፊት የየካቲት አብዮት በግብታዊነት በመፈንዳቱ ጨለማ ለብርሃን ቦታውን ይለቅ ዘንድ ተጣድፎ መጓዝ፣ በትግሉ አውድማ በተግባር መገኘትና ትግሉን ለመምራት መጣርና መዋደቅ የግድ ሆነበት::*

*ኢሕአፓ የሀገሪቷን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ወርሶ በጠራ ሀገራዊ ፍቅር እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ እልህ አስጨራሽና ብዙ መስዋእትነትን የሚጠይቁ ጥረቶች አደረገ እንጂ የሀገር ችግሮችን በራሱ*

አልፈጠረም። አርሶ አደሩ በገባርነት ተቀይዶ ሲማቅቅ ስለነበር መሬት ለአራሹ ብሎ መነሳትና ለችግሩ መፍትኄ መፈለግ የግድ ነበር። ሥርዓቱ የጥቂቶች ሆኖ ብዙኀኑ በመከራና ድህነት ይጠበሱ ነበርና ይህ ይወገድ ማለት አስፈላጊ ነበር። በብሔረሰብና በሃይማኖት ልዩነት ነበርና ይህም ለሀገር አንድነት አይጠቅምም ብሎ መፍትኄ መሻት ለሌላ ትውልድ የማይለጉት ግዳጅ ነበር። የኦሮሞ ህዝብ ትግል፤ ሜጫ ቱለማ--ባሌ የዋቆ ጎቱ እንቅስቃሴ፤ የኦጋዴንና የኤርትራ ችግሮች ሁሉ በስርዓቱ ተቀፍቅፈው የመፍትኄ ያለህ ብለው እየጮሁ ነበሩና ሀገርን ከጭቆናና ብዝበዛ ነፃ አውጥተን ዴሞክራሲን እናስፍን ብሎ የተነሳ ኃይል ይህን ሁሉ ችግር አላየሁም ብሎ ማለፍ አይችልም ነበር። ቀደም ብለን ገልፀን እንደነበረው “የተለያየውን አገናኝቶ፤ የተሰበረውን ጠግኖ፤ የተሰነጠረውን አያይዞ፤ ያፈነገጠውን አስማምቶ፤ የተበተነውን ለቅሞ፤ ባጭር ቃልም ሀገርን በአዲስ መልክ የማስተናበር ገና በሩቁ የሚያስፈራ እጅግ ከባድ ዕዳና ኃላፊነት ቢሆንም ” ኢሕአፓ ግዳጁን ሳይፈራ ተቀብሎ የአቅሙን ለመወጣት ጥሯል። ሆነም ቀረም ኢሕአፓ በነበረው ራዕይ መሠረት ለችግሮች መፍትኄ ሊሰጥ ተነስቶ ታግሎ ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት ከፍሏል። በየካቲት አብዮት ፍንዳታ ወቅትም ድርጅቱ የመሪነቱን ሚና ለመያዝ አቅሙ ገና ባይፈቅድለትም ያን ታሪካዊ የሕዝብ ትግል ፈር ለማስያዝ ወይም ለማጠናከር የተቻለውን ሁሉ አድርጓል። በገዋ ላይ፤ ከሕዝብ አናት በላይ ሆነው የሚንሳፈፉ መፈክሮችን ሳይሆን የሕዝብን ስሜት በትክክል የሚያስተጋቡና ምኞቱን የሚያንፀባርቁ፤ መሠረታዊና ወቅታዊ ችግሮቹን የሚመለከቱ መፈክሮችን አንስቶ እንታገል በማለቱም ኢሕአፓ የሕዝብን ሙሉ ድጋፍ አገኘ።

ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስረሳ ሆነና የአፄው ስርዓት ከከፋው በበለጠ የአምባገነኑ ደርግ-ኢሰፓ አገዛዝ በመከፋቱና ዛሬም ደግሞ ሀገርን ራሷን ስረ መሠረቷን ሊያናጋና ሊያጠፋ የተነሳ ጠባብ ብሔርተኛ አምባገነናዊው ቡድን በመከሰቱ ያለፈው የተሻለ ነበር የሚል ስሜታዊ ግምት ቢደመጥም ለብዙኃኑ ያ ሥርዓት አስከፊና መጥፎ፤ ብዙሀኑን መቀመቅ የከተተ ነበር። በነበረው ተጨባጭ ሁኔታም አሜሪካ ከአፄው ስርዓት ጎን በመቆሟ /ዛሬም ከወያኔ ጎን እንደተሰየመችው ሁሉ/ ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም የነፃነት ትግሎች ጠላትና የደቡብ አፍሪካ ዘረኛው ስርዓት የአፓርቴይድ ደጋፊ የነበረው ይኸው አሜሪካ ስለነበረ ስር ነቀል ለውጥ ፈላጊው ክፍል፤ ለአንዴም ለሁሌም ለእድገት የእግር ካቴና የሆነውን ስርዓት ማስወገድ የፈለገው ተራማጅ ክፍል ወደ ግራው ማዘንበሉና የትግል ወዳጆች ከሆኑት የሶሻሊስቱ ዓለም ጋር መሰለፉ አይቀሬ ሆነ ። ኢሕአፓ ወጣም ወረደም ኢትዮጵያን የምታኮራ ሀገር ለማድረግ የተነሳ ድርጅት ስለነበር በወቅቱ ማን ጠላት ማን ወዳጅ ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄም የሰጠው መልስ በዚሁ የተቃኘ እንደነበር ሊዘነጋ የሚችል አይደለም። መሬት ለአራሹ ሲል፤ ለብሔረሰቦች እኩልነትና መብት ሲቆም፤ ሀገር ከባዕድ ተፅዕኖ ነፃ ትሁን ሲል፤ ጦርነቶች በሰላም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈቱ ሲል ወዘተ… መነሻው ያው የጋራ ሀገርን ለመገንባትና ጠላቶቿ ካጠመዱላት አዘቅት ለማውጣት ስለነበር የተጓዘበት መንገድ ቀና ሆነ ጠምዛዛ፤ ተሳሳተ ተባለ ጥሩ ስራ መንስዔው ግን ሁሌም ሀገሬን ኢትዮጵያን ልጥቀም ላጠናክር ብሎ መሆኑ በማንም በጥያቄ ሊገባ የሚችል አይደለም። ዛሬ ያንን የነበረውን መጥፎ ሥርዓት ቅዱስ ቅባት ረጭተው ሌላ ገፅታ ሊሰጡት የሚጥሩ ቢኖሩም ሐቁ ግን የሚያሳየው በሁሉም መንገድ በትግል ተወጥሮ መውደቅ አለበት የሚለውን ብቻ ነበር። በነፃ የመደራጀትን ፀጋ ተነፍጎ የነበረው ሕዝብ፤ ብረት አልባ የነበረው ሕዝብ ግን ተስፋ ያድናል ብሎ በቆራጥነት ባካሄደው ትግል ስርዓቱን ሊያፈርስ ችሏል። የኢሕአፓ ትግል የተካሄደው ከዚህ እምነት በመነሳት ነበረም ማለት ይቻላል--በሕዝብ አቸናፊነት ላይ ፅኑ እምነትን በመያዝ።

የሕዝብን ድል ቀምቶ በሥልጣን የተሰየመው የመኮንኖች ቡድን ውስብስቡን የሀገር ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች በጥይት ሩምታና በአዋጅ ጋጋታ እፈታለሁ ብሎ ሲያቅራራ ያመኑት፤ መንግስታችን መጣ ብለው የደገፉት፤ በሕዝብ ላይ የመቅሰፍት ተልዕኮውን ሊያዘንብ ሲዳዳ በርታ ግፋ ያሉት ጥቂቶች አልነበሩም። ኮሶ ላልቀመሰው ይመር አይመስለው ሆነና በ1983 ዓ.ም. ጠባቡ ህወሓት ሥልጣን ሲይዝ እስቲ ፀረ ህዝቡን የእነ መለስን ቡድን እንየው፤ ጊዜም እንስጠው እንዳሉት ሁሉ ለደርጉ ጊዜና አመኔታ ሊሰጡ የተነሱት ለደረሰው ሽብርና ፍጅት ድልዳል - ወደዱም ጠሉም- ማዘጋጀታቸው ከጊዜ በኋላ የተረጋገጠ ሐቅ ሆኗል። ኢሕአፓ የሕዝብ ድል መቀማቱን በመቃወም፤ ነቅቶ እየታገለ ያ ሕዝብ ሞግዚት አያሻውም ብሎ ጭቁኑን ሕዝብ ለወሳኝ ትግል ሲቀሰቅስና ሲጠራ፤ ከሁሉም የተውጣጣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም ሲል፤ አይዞህ በርታ ያላሉትና ከነበረው አገዛዝ ጋር የተሰለፉት ዛሬ ዞረው ሊተቹት መቃጣታቸውን ደግሞ እያየነው

እየታዘብነው ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ኢሕአፓ ሰላማዊ ትግል በተቻለበት እምቢኝ ብሎ ለጦርነት ያቆበቀበ አልነበረም፡፡ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከተከበሩ በሰላም እታገላለሁ ብሎ በፕሮግራሙ ያኔም እንደዛሬው ቢያረጋግጥም አድማጭ አላገኘም፡፡ የሕዝብ ድምፅና ትግል ሚዛን እንዲደፋ በጋራ ሲተም ውጤታማ ይሆናል ብሎ የሚያምነው ኢሕአፓ ለኅብረት ሂደትም የሰጠው ምላሽ ሁሉን አቀፍ ይሁን የሚል እንጂ የጭፍን እምቢታ እንዳልነበረ በወቅቱ ይፋ ባደረጋቸው አቅዋሞች ተመዝግቦ ያለ ነው፡፡ የፖለቲካው ሁኔታ በችኮላና በእልክ ወደ እማይፈለግና መጥፎ ሁኔታ እንዳያመራ በሚል ከደርግም ሆነ ደርግን በሂስ እንደግፍ ከሚሉት ቡድኖች ጋር ውይይት ለማካሄድ የማይናቅና የማይታበል ጥረት ቢያደርግም ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን በውሱን ድርጅታዊ ጥቅም/ሹመት ለመለወጥ ባለመፈለጉና ከክህደት አቅዋም በመራቁ በጠላት ተፈርጆ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር የተባሉት ገደብ ያጡ የጅምላ ፍጅት ተግባሮች በአዋጅ ተካሄዱበት፡፡ ይህን ዓይነቱን ግድያ ለመከላከል ኢሕአፓ የወሰደውን እርምጃ የሽብሩ መንስዔ ነበር ብለው ጋሪውን ከፈረሱ በማስቀደም ሀሰትን ሊያሰራጩ የሚጥሩ ቢኖሩም ሕዝባችን የሚያውቀው ሀቅ ግን ሕዝብ የደገፈውን ኢሕአፓ ለማጥፋት ደርግና አጋሮቹ ሽብር ማካሄዳቸውንና ትውልድ መጨረሳቸውን ነው፡፡

ኢሕአፓ 35 ዓመት ሆነው ስንል በደፈናው ጊዜ ቆጠራ ሳይሆን የትግል ታሪክን የምናነሳበት፤ ሰማዕትን የምንዘክርበት፤ ለቀጣዩ ትግልም አቅጣጫ የምንሰጥበት ነው፡፡ ሀገርን መውደድ፤ ለሀገር ህይወትን መለገስ፤ የትግሉ ነው ህይወቴ ብሎ መራራውን የትግል ውጣና ውረድ መቋቋም ቀላል እንዳልሆነ ቢያንስ ትግል ብለው ጀምረው መከራውና ግዳጁ ያቃታቸው የሚያውቁት ነው፡፡ ያለፈው ቢቀር በእነ መለስ ዜናዊ ጊዜ ተቃዋሚ ነን ብለው ሁኔታው ጠጠር ሲል ሸብረክ ብለው፤ ያለመከራ አይገኝ እንጀራን ረስተው፤ የሕዝብና የሀገርን አደራ በመዘንጋት የሕወሓት አስተዳደር ጋር መሥራት የመረጡትን በምሳሌ መጥቀስ እንችላለን፡፡ የ35 ዓመት ፅናት ትምህርታዊነቱ በዚህ መልክ ከፍተኛ ነው፡፡ ኢሕአፓ የአገዛዞችን ድለላ አልሰማ ብሎ፤ የሕዝብን ሥልጣንና የበላይነት በማስቀደሙ ለአምባገነኖች የድለላ ሆነ ድንፋታ ዘመቻ ሰለባ አልሆነም፡፡ የመጣውን አገዛዝ ሁሉ መንግሥታችን መጣ፤ የአርሶ አደሩ የብዙሀኑ አገዛዝ መጣ እያሉና እያገለገሉ የሕዝብን ትግል ጎድተው ራሳቸውንም ከውድቀት ሊያድኑ ያልቻሉ ከዚህ የኢሕአፓ የፀና አቅዋም መማር በቻሉ ነበር፡፡ ግን ይህ አልሆነም፡፡ ደርግ ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ ይል የነበረውን ሕዝብና ድርጅት ማዳመጥ ያልፈለጉ በመኖራቸው የሕዝብ ጎራ ሊሆን የሚችለው ተከፋፍሎ ለአረመኔዎቹ ሽብር አመቺ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ጊዜ አለፈ በሚል፤ ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ የሚሰብር የመሰላቸው ዛሬ ያንን ግፍና ወንጀል ክደው አለህፍረት ኢሕአፓ ነው በዳዩ እያሉ ቢወራጩም ታሪክ በማይፋቅ መንገድ የመዘገበው ሀቅ ግን የሕዝብን ትግል ለማውደም ሥርዓቱ አሰቃቂ ሽብርን ማካሄዱን ነው፡፡ በፖለቲካው ትግል መስክ ኢሕአፓ አቸናፊ በመሆኑ አገዛዙ ራሱን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ይሠራልኛል ያለው ብቸኛ መድኃኒት ሺዎችን በሽብር መጨፍጨፍ ነበር፡፡ በዚህ ተፈታታኝ ጊዜ ኢሕአፓ ሀገርና ወገን የጠየቀውን መስዋዕትነት ከፈለ እንጂ ወገቤን ብሎ፤ ራሴን ላድን ብሎ አልሸሸም፤ ከነበረው አረመኔ አገዛዝ ጋር ሊሞዳሞድም አልጣረም፡፡ አባላቱ ብቻ ሳይሆኑ የአመራር አባላቱ ከተስፋዬ ደባሳይ እስከ ክፍሉ ከበደ፥ እነ ዮሐንስ ብርሃኔ፥ ፅኑ አባላቶችም እነ ይትባረክ፥ወብሸት፥ ዘርዓብሩክ፥ ፍቀሬ ዘርጋው፥ ተካልኝ ወልደ አማኑዔል፥ ኢንጂኔር ኦስማን፥ ሱራፌል ካባ፥ አህመድ ነጋሽ፥ ፈትህልዲን ጅብሪል፥ ገነት ማዘንጊያ፥ ሙጂብ ስሩር፥ ገላዬ ፈይሳ፥ ኢብራሂም ዳውድ፥ ወታደር ሲሳይ ወልደ ማርያም፥ መቶ አለቃ ታምራት ወልደ ማርያም፥ ማርቆስ ሀጎስና ሺዎች ሁሉም ለሀገር ተሰውተዋል፡፡ የህወሓትን ጠባብና ፀረ-ሕዝብ ቡድን በመቃወም የሕይወት ዋጋ እንደከፈሉት እንደነ ገመቹ፥ ጋይም፥ ገለብ ዳፍላ፥ ዋሲሁን፥ ግርማ፥ መስከረም፥ አምባዬ፥ ጃብርና ስንቶቹ ማለት ነው፡፡ እምነት ከተባለ፥ ትግል ከተባለ ትግሉ የሚጠይቀውን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆን እንደሚያሻ ኢሕአፓ በተጨባጭ 35 ዓመት ሙሉ ማስተማሩ ደግሞ የማይካድ ነው፡፡ ኢሕአፓ 35 ዓመት ሞላው ስንልም ይህን ተመክሮ እየዘከርንና ተገንዝቡትም እያልን ነው፡፡

ኢሕአፓ በሀገራችን የመጀመሪያው በአዲስ መንገድ የተደራጀና ራሱንም በይፋ ያሳወቀ ድርጅት በመሆኑ ሊማርበት የሚችል የሀገር ተመክሮ አልነበረውም፡፡ የባዕዳኑን ቢያጤንም የሀገሩ ባለመኖሩ እየታገለ መማሩ፤ እየተሳሳተ በሂደት መታረሙና በዚያውም ትግል ሁሌም ዋጋ ይጠይቃልና በስህተቱም መጎዳቱ አልቀረም፡፡ ይህንን በተመለከተ በሚያዝያ 1971 ባወጣው ዴሞክራሲያ ( "በግምገማ እርማት ፤ በግለሂስ እድሳት" ) በስፋት አስረድቷል፡፡ የድርጅት ማንነት ሆነ ጠቃሚነት የሚገለፀው ሁኔታዎችን አጢኖ መደረግ ያለባቸውን ለውጦች በጊዜ ማድረግ ሲችል፤ ከስህተቱ

ሲማር፣ ተስተካክሎ ለመጓዝ ሲጥር ነው:: ኢሕአፓ አቅዋሞቹ ከተጨባጩ ሁኔታና ከሕዝብ ፍላጎት ወይም ተመክሮ ካሳየው ጋር ባልገጠመበት ለመታረም ጊዜ አልወሰደም:: የጠባብ ብሔረተኛነትን አደጋ በጊዜ ተገንዝቦ የእነ መለስ ስብኃት ነጋ ቡድን ትግራይ ትገንጠል፣ ሁሉም ብሔረሰቦች የራሳቸውን ነፃ መንግስት ያቋቁሙ ብሎ ገና ከመጀመሪያው ማኒፌስቶ/ፕሮግራም ካወጣ ጀምሮ ጥበትንና ግንጠላን ታግሏል:: ለዚህም የደም ዋጋ ከፍሏል-- ከ30 ዓመት በፊት ማለት ነው:: ኢሕአፓ የወያኔና የጠባቦችን ጎጂነት አውቆ መታገል የጀመረው ህወሓት ለሥልጣን ሲበቃ ወይም ከዚያ ወዲህ አይደለም:: በዚህም የተነሳ ይህ ጠባብ ቡድን በተናጠልም ሆነ ከባዕድ አጋሮቹ ጋር በመሆን በኢሕአፓ ላይ በተደጋጋሚ ዘምቶ ለበርካታ ሕይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል:: ህወሓት ተብዬው ድርጅት የአልባኒያው አምባገነን መንግስትና የስታሊን ማለትም የጭፍን አምባገነንነት አዳናቂ ሆኖ ግራ ክንፍ ነኝ፣ ማሌሌት ነኝ፣ 10 ዓመት ኮሙኒሰት ሆኜ ተጉዣለሁ ወዘተ ብሎ ሲባርቅ ኢሕአፓ ከዚህ ዓይነቶቹ ፅንፈኛና አምባገነናዊ አቅዋሞች በመራቅ፣ ገና የበርሊን ግንብ ሳይፈርስ የሶቭየትና ምስራቅ ጀርመን ሂደትና ራዕይ የማይጠቅም መሆኑን ገልፆ በ1976 ዓ.ም. በነፃ ቋራ ባካሄደው ሁለተኛ ጉባዔ አቅዋሙን አስተካክሎ ይፋ ወጥቶ ነበር:: የኤርትራ ችግር በፌዴሬላዊ ግንኙነት ይፈታ፣ የመገንጠል አማራጭ ጎጂ ስለሆነ ይተው፣ መሬት ለአራሹ በባለቤትነት ይሁን ወዘተ... ብሎም የወጣውና የታገለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ነው:: ይህ ሁሉ ታሪክ ነው፣ የሚታወቅና የተመዘገበ -- ማንም ሀሰትን በመደጋገም ሊሽረው የማይችል ሐቅ::

ወደ ነበረው መለስ ብለን ስናይ ደግሞ እንደ ኢሕአፓ ጥቃት የበዛበት፣ ሽብር የተካሄደበት፣ በርካታ ኃይሎች ሊያጠፉት የተረባረቡበት ድርጅት የለም ብንል ማጋነን አይሆንም:: ላይችል አይሰጠውም ሆነና ድርጅቱ ወደቀ ሲሉት እየተነሳ፣ ጠፋ አከተመለት ሲሉ እያንሰራራ ቀጠለ እንጂ የተሰነዘረበት ዱላ፣ የተካሄደበት አረመኔያዊ ሽብር ቀላል አልነበረም:: የመከራ ሌሊት አያልቅም ዓይነት ሆኖ በነፃ እርምጃና በቀይ ሽብር ያን ሁሉ ግፍና መከራን የተቀበለው ማን መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያውቀው ሐቅ ነው:: ነፃ እርምጃ ቀይ ሽብር፣ የጠባቦች ወረራና ጥቃት፣ ከውስጥ የፈለቁ አፍራሽ አንጃዎች፣ ዳግም የጠባቦች ወረራ፣ እንደገና የህወሓትና የሱዳን ወዘተ ጥቃት-ኢሕአፓ ይህ ነው የማይባል ጎጂና አጥፊ ዘመቻ ተካሂዶበታል:: ግን ዕብሪት÷ ጠባብነት÷ አምባገነንነት የተባሉትን ተውሳኮች ከተቸነከሩበት ነቅሎ ለማስወገድ ደም ገብሮ እያንሰራራ ይኸው እስካዛሬ ህልውናውን ጠብቆ በትግሉ መስክ አለ:: አጥፍተነዋል ብለው ያልደለቁ፣ ህልውናው ጠርዝ ላይ ነው ብለው ያልተሳለቁ፣ አለ አንዴ ብለው ውርርድ ሊገቡ ያልተጋበዙ፣ የጥፋት ፃዕረ ሞት ወስዶታል ብለው የለፈፉ፣ አበቃለት ያላሉ ጥቂቶች አልነበሩም:: ሁሉንም ግን ኢሕአፓ አሳፍሯቸዋል:: ከወደቀበት እየተነሳ፣ የሕዝብን ሰንደቅ ፀንቶ እያውለበለበ፣ ለሹመትና ለከርስ ሳይገዛ፣ በዙፋንና ወንበር ላይ ማንኛውም ወሮበላ፣ ቁንጫና ትኋንም ቢሆን ሊወጣ እንደሚችል ተገንዘቦ፣ ሁሉን መከራ ተቋቁሞ፣ ህልውናውን ጠብቆ ዛሬም ለሕዝብ ጠላት እሾህ ሆኖ እየታገለ ነው:: ዝነኛው ገጣሚ ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ እንዳለው ፤

ስንቱን ፈተና አልፎ በሚያስደንቅ ትዕግስት<br>
ለትግሉ ድቁና ሆነ ቅስና ኋላም በምንክሱናው ዘመናት<br>
ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ሲዘጋጅ ለብቃት<br>
ዛሬ ቢያወሩልኝ አልሰማም የሻገተ ወሬ የቀመለ<br>
ድፍን ሀበሻ ቢቀላምድ እንዲህ እንዲህ እያለ<br>
ገዳሙን ትቶ ኮበለለ<br>
ይህአባ ቆቡን ጣለ ::

ኢሕአፓ ጠላት የበዛበት የጠላት ያለህ ብሎ ነጋሪት ስለጎሸመ ሳይሆን ባለው ፅኑ ኢትዮጵያዊ አቀዋም የተነሳ ከሀገራችን ጠላቶች ጋር ስለተጋጨ ነው:: እንደነ መለስ ቡድን ኤርትራ በኢትዮጵያ በቅኝ ግዛትነት ተይዛለች ብሎ ከታሪክ ተጣልቶ ድጋፍን አልፈለገም:: ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያን የሶማሊያ ግዛት ነው ብሎ አልፈረመም:: እንደ ከሀዲው መንጋ ከሱዳን ተስማምቶ የሀገርን ጥቅም ጎድቶ አልተንቀሳቀሰም:: ምዕራቦችን ለማስደሰትና ገንዘባቸውን ለማግኘት ሲል ሀገርና ወገንን አልሸጠም:: ታክቲክ ወይም ዘዴን ማወቅ ተስኖት ሳይሆን ሀገርን ሸጦ ድርጅትን መጥቀም የሚሉት ፈሊጥ አልዋጥለት በማለቱ ነው::

የትግል መጨረሻው የፖለቲካ ሥልጣንን መያዝ ነው የሚል የተለምዶ አነጋገርና አቅዋም አለ። የዚህ እውነታ የሚካድ አይደለም-- ሕዝባዊ ፕሮግራምን እውን ለማድረግ ስልጣን መያዝ ያስፈልጋል። ተገቢው ሥልጣን ሊያዝ የሚችለው ግን ሥልጣን ከሕዝብ ሲመነጭ ነው። በሕዝብ ፍላጎትና ምርጫ ወደ ሥልጣን ሲወጣ ነው። የመጨረሻ ድል ተገኘ ሊባል የሚችለውም ሕዝብ የመብቱ ባለቤት ሲሆን ነው። ኢሕአፓ ሥልጣን መያዝ አለመቻሉ የሕዝብን ትግል ሽንፈት አረጋጋጭ አይደለም። ኢሕአፓ ትግል ከጀመረ ጊዜ አንስቶ እሳካሁን የሕዝብ ትግል ብዙ ድሎችን ተቀዳጅቷል። የድርጅትን ማንነትና ምንነት፥ ጠቀሜታውን ሕዝብ ተምሮ እየተደራጀ ታግሏል። በኢሕአፓ ትግል ተማሪው፥ ምሁሩ ነጋዴው፥ ታክሲ ነጂው ጋሪ ነጂው፥ ላብአደሩ አርሶ አደሩ፥ ወንዱ ሴቱ፥ ክርስቲያኑ እስላሙ፥ ወታደሩ ሲቪሉ፥ አዛውንቱ ወጣቱ፥ በአጠቃላይ ከሁሉም ብሔረሰብ የተውጣጣ ሰፊ ሕዝብ የምንለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተሳትፏል። የገበየው ተመክሮ ሰፊ በመሆኑም እነሆ ዛሬ ለነመለስ አማባገነን አልገዛም ብሎ ሲያምፅና እምቢ ሲል፥ ያ እውቀቱና ልምዱ ምሰሶ ሆኖታል። ኢሕአፓም ለጥቅም ተገዝቶ፤ ለባዕዳንና ለባለነፍጥ ተሳንብሶ የሕዝብን ሰንደቅ ከትቢያ ባለመጣሉ፤ የዚህ ሕዝባዊ ትግልና ፅናት አርአያና ተከላካይ ሆኖ ለመቆየት ችሏል። ይህም ድል እንጂ ሽንፈት አይደለም። የሕዝባዊ ትግልን ሂደትና ውጤት በኳስ ጨዋታ ደረጃ በማየት ጎል አገባ/ግብ አገኘ አላገኘም፤ ተሸነፈ አሸነፈ ማለት የማይቻል መሆኑን ያልተነገነዘቡ ክፍሎች ለስልጣን የበቃ አሸናፊ ያልበቃን ተሸናፊና ዋጋ ቢስ አድርገው መደምደማቸው ስሕተት መሆኑ ግልፅ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አለመቸነፍ አንዱ ማስረጃ ኢሕአፓ ዛሬም በትግሉ ፀንቶ መቀጠሉም ነው ማለት ይቻላል። የትግል ሻማ እስካልጠፋ ድረስ ድልና ሽንፈት ገና የመጨረሻውን ውሳኔ አላገኘም ማለት እንችላለን። ኢሕአፓ ለዚህ ቀጣይ ትግል እምብርት ነው። ትግልን ትቶ በዳር ተመልካች ሆኖ ከንፈር መምጠጡና አበስኩ ገብርኩ ማለቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ቅንጦት እንደሆነ አምኖ እስካዘሬ በትግሉ ፀንቶም ቀጥሏል። የሀገር ህልውና ለአደጋ ተጋልጦ እያለ ደግሞ መቀናጣቱ ይቅርታ የማይደርግለት ጥፋት ነው።

ኢሕአፓ ባለፉት 35 ዓመታት ያሳፈለውን ተመክሮ እየጠቃቀሰና እየገመገመ፤ የጀግንነት ታሪኩን እያስታወሰ፤ የዚያ አኩሪ ትውልድ አታጋይነቱን እያነሳ፤ ስንቱ አጥፊ ከውጭም ከውስጥም ተነስቶበት ተቋቁሞ በመበርከቱ እየተኩራራ ይታደሷል እንጂ ይታገሏል እያለ የሚገሸር ድርጅት ሳይሆን ዛሬ ያለንበትን አስከፊ ሁኔታ በማጤን የትግል አቅጣጫን ወዴት ለሚለውም ምላሽ ሰጥቶ ለትግሉ አስተዋፅዖ ለማድረግ የሚጥር ድርጅት ነው። ኢሕአፓ ቀደም ተብሎ እንደተገለፀው ሁሉ ከደርግ እስከ ወያኔ ጥቃት ቢደርስበትም ፀንቶ የታገለውና ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ዓላማቸው እንዳይሳካለቸው የተዋደቀው ቀላሉ ጎዳና ሳይቀልለት ቀርቶ ሳይሆን-- ማለትም ላለው አገዛዝ ተለሳልሶና ተመቻችቶ መቅረቡን ሳያይ ቀርቶ ሳይሆን-- የሕዝብ ትግል ግቡን እስኪመታ ደረስ መግፋት ግዴጅ ነው ብሎ በማመኑ ነው። ብልህነት የሕዝብን ፕሮግራም ፀንቶ መግፋቱና መቆሙ ሳይሆን በሁሉም አጋጣሚ ለገዢው ቡድንና ለባዕዳን መለስለስና የወረቀት ነብር መሆኑ የሚመስላቸው በእርግጥም ኢሕአፓን ቢኮንኑና ግትርም ቢሉ አስገራሚ አይደለም። እጅ ተወርች የታሰረው ሕዘባችን መከራና ዕጣው የማይቆረቁራቸውና ከደርግም ሆነ ከዘረኛው የዛሬ ቡድን ጋር ሊተቃቀፉ የሚፈልጉት፤ በአገዛዙ ፍቃድ ወይም ከጨቋኞች አብረው በግል ሊጠቀሙ የሚፈልጉ ሁሉ እንደ ኢሕአፓ ዓይነቱን በፀረ ጠባቡ ህወሓት አቅዋም የፀናውን ክፍል ባይወዱ አስገራሚ አይደለም።

ኢሕአፓ የዛሬን የትግል ይዘትና አቅጣጫ በተመለከተ ከምን ደርሰናል ምን ማድረግ ይገባናል ሲል ደግሞ ለዓመታት ጠባዩን ተግባሩን ያወቀውን የነመለስን ጠባብና ዘረኛ ቡድን በተመለከተ ምንም ብዥታ ሳይሰፍን ግንዛቤና ድምዳሜ እንዲኖር ይፈልጋል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ፀረ-ኢትዮጵያ ለመሆኑ ምስክር ማስረጃ መጠየቅ ዛሬ ከቶም አያሻም። ይህ ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን ፀረ ሕዝብነቱን በደም ተጨማልቆ ያስመሰከረ ነውና አምርረን ታግለን ልናስወግደው በሚገባን ወቅት ስብር፥ ጎንበስ እያልን በመፍትኄ አካልነት ልናየው ወይም አልፎ ተርፎ በቀደደው ቦይ ፈሰን ዛሬም ልንጃጃልለት አይጠበቅም። የግንቦት 97 ምርጫና የተከተለው ሁሉ የመለስ አገዛዝ ማንና ምን መሆኑን በግልፅ ዳግም አሳይቶናል። ተቃዋሚ ካልንም ደግሞ የብዥታ ሰለባዎች ሆነው በተገኙበት የደረሰውን ጉዳት አይተናል። የ35 ዓመት የትግል ተመክሮ የሚያረጋግጥልን ሀቅ ከፀረ ሕዝብ አገዛዝ መቸም ቢሆን መቸ ደግ ነገርን መጠበቅ እንደማይቻል ነው። ያለው ሁኔታ ባለበት እየቀጠለና የሀገር ችግሮች ጊዜ ባገኙ ቁጥር እየተባባሱ ሲሄዱ፤ የሌለን ለውጥ አለ ብሎ ለመጪው ምርጫ ተዘጋጁ ብሎ ጥሪ ማድረግ ከንቱነት ነው። ከመለስ አገዛዝ ዕርቅና ሰላምን መጠበቅ ሞኝነት ነው። ፀረ ኢትዮጵያ ከሆኑ የሀገርም ሆነ ባዕዳኖች የሚጠበቅ ደግ ነገር ባለመኖሩ ለእነዚህ ክፍሎች ጆሮን መስጠት ጎጂ ስህተት መሆኑን

ኢሕአፓ ከማሳሰብ ተቆጥቦ አያውቅም:: በ35 ዓመት ታሪኩ ኢሕአፓ የተገነዘበውና ለሌሎችም የሚጠቁመው ሕዝባዊ ሀቅ ካለ የሀገሩን ጥቅም ጠባቂ ራሱ የሀገሪቷ ሕዝብ ብቻ መሆኑን ነው:: ባዕዳን ወጣም ወረደም ቅድሚያ ሰጥተው የሚጠብቁት የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ነው--በዚህም ልንወቅሳቸው አይገባም:: እኛም ብሄራዊ ሀገራዊ ጥቅማችንን ማስጠበቅ መቻል አለብንናም ነው:: የመለስ አገዛዝ ደግሞ ለማደናገር የበግ ለምድ ቢለብስ ቋሚና ዘላቂ ጠባዩ ግን ተኩላ ፀረ ሕዝብነት መሆኑን ቃሊቲም፥ ዴዴሳም፥ ዝዋይም እንዲሁም ግድያውም፥ ስየሉም፥ ሰቆቃውም ሁሉ ያሳያል:: ስለዚህም ላለፈው አንፀፀትም ብንል እንኳን ለሚመጣው አለመበለጥ ደግሞ የግድ ይሆናል::

ይህን በባዕዳን ድጋፍ በሥልጣን የተሰየመውን ሀገር አጥፊ ቡድን በተመለከተ ኢሕአፓ ቡድኑ ከተመሰረተ ጀምሮ ጠባብ ብሔረተኛው ቡድን እንገንጠል አቅዋሙ መዘዘኛ መሆኑን በማጋለጥ ጉዳት ቢያስከትልበትም ታግሎታል:: የሀገር አንድነት ይሁን ስለተባለ የሚረጋገጥ አይደለም:: ትግልን፥ ሕዝብ ማሰባሰብን ይጠይቃል:: ከትምክህትና ጠባብነት የተፃረረ አቅዋም ይዞ ሕዝብን መቀስቀስና ማደራጀት ያስፈልጋል:: የሀገሪቷ ውስብስብና ከባድ ችግሮች የጋራ ጥረትን፤ የሕዝብን ሀሉ ርብርቦሽን ይጠይቃሉ ብሎ ያመነው ኢሕአፓ ለዓመታት--ሀቁን ለመናገር ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ-- በኅብረት ኬሌሎች ኃይሎች ጋር በእኩልነት መቀናጀት ለመታገል ሳይታክት ጥሯል:: የአንድ ድርጅት ብቸኛ ትግልና የድል ምኞት በጋራ፥ የሁሉም ትግል ቢተካ ውጤቱ የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት ነው ኢሕአፓ ያለው:: በዚህ እምነቱም ደም ከተቃባቸውም ጋር ሳይቀር ለሀገር ሲል፤ የሀገርን ጥቅም በማስቀደም አብሮ ትግሉን ለመግፋት ጥሯል:: ዛሬም ቢሆን የድልን አቅጣጫ ኢሕአፓ ሲያመለክት፤ በኅብረት የመታገልን አስፈላጊነት ጫና ሰጥቶ፥ ከክፍፍልና አጓጉል ፉክክር በመራቅ፥ በጋራ ጠላት ላይ ርብርብ ማድረግ የሚለውን ተቀባይነት እንዲያገኝ ይታገላል::

በሰማዕት ደም የተገበየ ተመክሮ ለትግል ካልጠቀመ አሳዛኝ ነው በሚል የሚያሳስበውም የዚሁ ምልክት ነው:::: ተወደደም ተጠላም ኢሕአፓ የኢትዮጵያ ሕዝብ የትግል ታሪክ ቅርስ ነው:: መቶ ሺዎች የተሰዉበት፤ ወጣት ሽማግሌ የተሰለፈበትና ከእንባ እስከ ደም የተገበረበት ድርጅት ነው:: የለም ጠፍቷል የሚሉትም ሳይቀሩ ሳይወዱ መኖሩን ማወቅ ተገደዋል:: ሀቁ ይነገር ከተባለ ደግሞ የመለስን አገዛዝ በብዛት የሚያቃዣው ካለ ኢሕአፓ ለመሆኑ ምንም ክርክር አያሻውም:: ይህም የሆነበት ዋና ምክንያቱ ኢሕአፓ የመለስን ቡድን ማንነት፤ ምንነትና ጠባይ የሚያውቅ ከመሆኑ ሌላ ለእኑ መለስ ድለላ የማይበገርና የፀና ኃይል በመሆኑ ነው:: የመለስ አገዛዝ ሲሻው ኢሕአፓ ደብዛውም የለ ቢልም ፀረ ኢሕአፓ የደህንነት ልዩ መምሪያ አቋቁሞ፤ ድርጅቱን በሌለበት ሳይቀር አየሁ ብሎ መደናበሩ የሚደበቅ አልሆነም:: ኢሕአፓ ደግሞ ፀረ ሕዝቦችን ማቃዠት ብቻ ሳይሆን ማውደም ግዳጄ/ግዴታችን ነው ብሎ እየታገለ ነው::

ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከመቸውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ ላይ እንዳለች የሚታይ ነው:: የባጀው ድህነትና መከራ ብሷል:: ዛሬ በሁሉም መስክ የከፋና የከረፋ አገዛዝ በሀገሪቷ ላይ ጉብ ብሏል:: በከተማም ሆነ በገጠር ሕዝብ እየተሰቃየ ነው:: የዛሬው የባሰ ክፋቱ ደግሞ ሀገርን ራሷን ሊያደባይ ይሁነኝ ብሎ የተነሳ አገዛዝ መሆኑ ነው:: ኢሕአፓ ሲመሰረት የተነሱ መሠረታዊና ቀዳሚ ሕዝባዊ መፈክሮች ዛሬም ወቅታዊ ናቸው:: መሬት ለአራሹ፤ ዴምክራሲ ለሰፊው ሕዝብ፤ የሀገር ሉዓላዊነት ይከበር፤ ሰርቶ አደሩ አይበዝበዝ፤ የብሔረሰቦች እኩልነት እውን ይሁን፤ የሀገር ዴሞክራሲያዊ አንድነት ይረጋገጥ፤ የሴቶች እኩልነትና መብት ይከበር፤ የሕግ የበላይነት ይረጋገጥ ወዘተ የሚሉት ዛሬም ምላሽ ጠያቂ ሆነው አሉ:: የጨቋኝ ሥርዓት አዳናቂ የነበረው የመለስ ቡድን ጭፍን አምባገነናዊ አገዛዝን በሕዝብ ላይ ጭኗል:: የባዕድ ሎሌና ቡችላ ሆኗል፤ የሀገር መሬትን ለባዕድ ጦር አሳልፎ ሰጥቷል:: ባዕድ አዞት የሰው ሀገር ወሮ ብዙ መቶ ኢትዮጵያዊ ሕይወትን ገብሯል:: በሀገሪቷ በሞላ የአፈና ሥርዓቱን ጭኗል:: ይህን ሽብርተኛ ቡድን ለመቋቋም በየመስኩ ረጅም ትግሎች ተካሂደዋል፤ ብዙ ሺ ዜጎችም በየአቅጣጫው ወድቀዋል:: ይህ የትግል ሂደት ራሱ በአዲስ ለሕዝብ ተመክሮን ለጋሽ ነውና እንማርበት ካልን ደግሞ ይህን ፀረ ህዝብ አገዛዝ ለማስወገድና ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳን በጋራ ለመታገል መቻልና በሁለ ገብ ትግልም፤ ሁኔታው ግድ በሚለው ስልት ሁሉ አገዛዙ ላይ መረባረብ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳናል:: የጋራ በሆኑት መሠረታዊና ሉዓላዊ እምነቶች ላይ በመመርኮዝ፤ በዚህ ዙሪያ በመሰባሰብ፤ መፈራቀቅን አስወግደን፤ በብሄረሰብና ሀይማኖት አገዛዙ ሊከፋፍለን የሚጥረውን ውድቅ አድርገን፤ የየግል ውሱን ድርጅታዊ ምኞቶችን ሳይሆን በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ መሠረት

ማድረግ የምንችላቸውን፣ ማድረግ ያለብንን አስቀድመን መተባበርና በጋራ በሥርዓቱ ላይ ጠራርጎ ወሳጅ ጎርፍና ማዕበል ለመሆን መጣጣር አለብን፡፡

ኢሕአፓ በ35 ዓመት የትግል ጉዞው ህልውናውን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግልም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አደርጓል፡፡ በሕዝብ ላይ በምርጥነት ሳይሰየም፣ ወደፊት ተስፈንጥሮም ከሕዝብ ሳይነጠል ወይም እየተጎተተ ትግልን ሳያቀዘቅዝ፣ የሕዝብን የህዋስ ንዝረት እያዳመጠና ከወዝ ጠረኑ እየተዛመደ ከሕዝብ ጎን ሆኖ መስዋዕትነትን ከፍሎ የታገለ ድርጅት ነው፡፡ ነባራዊ ሁኔታው ግድ ሲልም እየተስተካከለ፣ ፕሮግራሙን አቅዋሙን እያደሰ ቢሄድም ለኅብረሰባዊ ሰፊ ዴሞክራሲ ወይም ሶሻል-ዴሞክራሲ ቆሞ ያለው ኢሕአፓ ዛሬም ቢሆን ለሰፊው ሕዝብ መብትና የዴሞክራሲ ባለቤትነት፥ ለኢትዮጵያ አንድነት፥ ለሕዝቦቿ ዕኩልነትና ወንድማማችነት፥ ክብርና ትልቅነት የሚታገል፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅት ነው፡፡ ኢሕአፓ የሕዝብ ነውና ማንም ሆነ ማን ሊያጠፋው መቸም አልቻለም፣ አይችልምም፡፡

## ኢሕአፓ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያቸንፋል!!